International Ethiopian Woman Organization IEWO

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)

IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA

# ሴቶች በግፍ መደብደብ፤ መገደል አለባቸዉ እንዴ?

የኢትዮጵያ ሴቶች በዓለም ዙሪያ ተደብድበዉ ሞተዉ ይገኛሉ። ከሞት የሚድኑት ደግሞ በደረሰባቸዉ ጥቃት የተነሳ በጣም ይጎዳሉ፤ በሽተኛ ይሆናሉ ፤ ኑሮዋቸዉንም ለመቀጠል እክሎች ይገጥሟቸዋል። ይኽንን ሁኔታ ማስቀረት የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት መሆን አለበት፤ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህረሰቦች፤ የሃይማኖት ተቋማት፤ ብሎም ሌሎች ስብስቦች ይኽንን አሰቃቂ እና አሳዛኝ ሁኔታ ተመልካች በመሆን ሳይሆን ጉዳዩ ብለዉ በሚገባ መታገል ይኖርባቸዋል። ችግሮች ሳይፈጠሩ በፊት ቅድመ ዝግጅት፤ ትምህርት የመስጠት ሃላፊነትና ግዴታ የሁሉም መሆን ይኖርበታል። ችግር ከተፈጠረ ቦኋላ መወያየትና መፍትሄ መፈለግ ይጠበቅብናል። ከተቻለ ደግሞ ይበልጥ የሚጠቅመዉ ገና ከመጀመርያዉ ሁነታዎች ሳይባባሱ መኮራረፍና መራራቅ ሳይከሰቱ በፊት ባልና ሚስት  ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ አብረዉ ጊዜ ማሳለፋቸዉ አስፈላጊ መሆኑን ማስታወስ ነዉ።

በየጊዜዉ የሚያስደነግጡና እንዴት ከዚህ ደረጃ ላይ ሊደርስ ቻለ በሚያስብሉን አሳዛኝ ሁኔታ እህቶቻችን በኑሮ ጓደኞቻቸዉ፤ በባሎቻቸዉ ተደብድበዉ ይሞታሉ፤ በአጋጣሚም ሲድኑ የማይድንና የማይረሳ ጠባሳ ህይወታቸዉን ያበላሸዋል። ችግሩን አብረን መወያየት ስንጀምር ለተጠቃችዉ ወገን ማዘንና መቆም ሲገባ ለአጥቂዉ ስው ሰበብ ፈላጊዎች አይጠፉም፡ ደብዳቢዉ ሆነ ነፍሰ ገዳዩ ደህና ሰዉ አንደሆነ ይነገርለታል። ወደ መፍትሄ የሚወስደን ጥፋቱን ማቃለል ወይንም መካድ ሳይሆን ትክክል ያልሆነዉን አሳፋሪ ድርጊት ማጋለጥና ነዉርና ወንጀል መሆኑንም በገሀድ መናገር ስንችል ብቻ ነዉ።

በዉጭ አገር ኑሮ ዙሪያ ቤተሰብ፤ ዘመድ አዝማድ፤ ያገር ልጅ ወይንም ጎረቤት አለመኖራቸዉ ሽምግልናም የተለመደ ባለመሆኑ የሚያቃቅሩ ነገሮች በቀላሉ ሊከሩና ከመስመር ሊወጡ ይችላሉ። በየተሰደድንባቸዉ እካባቢዎች የሚገጥሙን ያልተለመዱ አኗኗሮች ወግና የባህል እለመጣጣም ከገመትነዉ በላይ ሊያስቸግሩን ቢችሉም ሁኔታዉ ወንዱንም ሴቱንም የሚነካ እንጂ በተለይ አንዱን ፆታ ብቻ የሚነካ አይደለም። በምንኖርባቸዉ አገሮች የተጎናጸፍናቸዉ መብቶች፤ የፈለግንበት መሄድ፤ ሃሳባችንን መግለጽ፤ ያሻንን አቋም መያዝ ወዘተ. በሞላ በመረረ ትግል የተገኙ መሆናቸዉን ለማወቅና ለማሳወቅ መጣር የሁላችንም ግዴታ መሆን አለበት። ያደግንባቸዉ ጎጂ ባህሎችን ለማስወገድ መታገል አለብን፤ ለሀይለኛ መንበርከክ፤ ሃይልን አለአግባብ መጠቀም፤ በደልን አይቶ እንዳላዩ ሰምተዉ እንዳልሰሙ መሆን፤ በይሉኝታ አመኻኝቶ ለሀቅ አለመቆም መቅረት ይኖርባቸዋል።

በግብረገብ ደረጃም ቢሆን ህብረተሰባችን የራሱን መለኪያዎች፤ አብረዉ የመኖርያ ዘዴዎች እያጣ ሲሄድ ከምንኖርባቸዉ አገሮች ጋራ ማዛመድም ሲያቅተዉ ዝም ብሎ መቀመጥና ማየት ተገቢ አይደለም። ችግሮች በዝተዉ ተጠራቅመዉ እስኪፈነዱ ድረስ ራስን ማፈን፤ ሰዎች ተጣጥመዉ አብረዉ መኖር ሲያቅታቸዉ ሌላ መፍትሄ አለመፈለግ፤ ከጭቅጭቅ ከንትርክ ብዛት ከጤንነት ዉጪ ከመሆንና ራስን ቤተሰብን የራስን ወገን ከመጉዳት መፍትሄ ወደመሻት ማዘንበል ያስፈልጋል። ፍጥጫዉ በዝቶ የተወጠረዉ አስኪፈነዳ ድረስ ብሎም

**IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA**

እስከማበድ ራስን እስከመሳት ድረስ መሄድ ለህብረተሰባችን ለልጆቻችን ብሎም ለራሳችን አስከፊ ወደሆነ መመለሻ ወደሌለዉ ጽንፍ መንጎድ ነዉ። ንዴትን መቆጣጠርያ ዘዴዎችን ማጤንና ለማሻሻል መሞከር እንጂ ወደ እልህና ወደ መጠጥ ብሎም ወደዱላ ማምራቱ አጥፍቶ ጠፊ ከመሆን አያድንም። ተለያይቶ በሰላም መኖርም እንደሚቻል መዘንጋት የለበትም።

አብሮ ለመኖር የትዳር ጓደኛ፤ የኑሮ ጓደኛ ምን ማለት እንደሆነ ማሰብ አዉጥቶ አዉርዶ ማሰላሰልን የግድ ይላል። እናቱን እህቱን የሚጠላ ወንድ የለም፤ ስለዚህም ሚስቱን ሆነ የኑሮ ጓደኛዉን ከእናትና ከእህቱ ይበልጥ ይሆናል እንጂ ያነሰ ቦታ ሊሰጣት አይገባም። የቤተሰብ አሰባሳቢ፤ ልጆችን አብራ አሳዳጊ፤ በመሆኗ ነዉ እኮ የትዳር ጓደኛ፤ የኑሮ ጓደኛ ተብላ የተሰየመችዉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የዜጎችን ሁሉ እኩልነት መቀበል፤ የሰዉ ልጆችን በሞላ የማይሻር መብት መገንዘብ ብሎም የሴቶችን ባለሙሉ መብት የሰዉ ልጅ መሆን መቀበል ማክበር ለራሳችን ህይወት ሆነ በአካባቢያችን ለሚያድጉ ልጆች ወሳኝነት አለዉ።

ይህንን መግለጫ ለማውጣት የተገደድንበት ዋና ምክንያት በተለያየ ጊዜ በሴቶች ላይ ጥቃት በመከሰቱ ሲሆን፣ አሁንም ባለፉት ሳምንታት ተመሳሳይ ጥቃት ስለደረሰ ይህንን ጉዳይ ህብረተሰቡ ትኩረት በመስጠት እንዲወያይበትና ወደ መፍትሄ ሃሳብ ለመምጣት እንዲችል በማሰብና ለማሳሰብም በሚል ነው።

መስከረም 25/ 2003

www.aesed.org

aesed.iewo@gmail.com